# የኢትዮጵያ ወጣት

የአድዋ ፤ የማይጨው ፤ የጥንት ጀግኖቹ
የምኒሊክ ፤ ካሳ ፤ ሞት አይፈሬዎቹ
ያደራው ፤ ቃል አለ ፤ ዛሬም በልጆቹ
የኢትዮጵያ ወጣት ፤ ነብር ፤ ትንታጎቹ
የሀገር አለኝታ ፤ ፊታውራሪዎቹ
ለባንዳ ለፋሽስት ፤ ውጋት አይመቹ ።

የኢትዮጵያ ወጣት ፤ የፋሽስት መጋኛ
በናት ሀገሩ ላይ ፤ ለሚያሾፍ ዘረኛ
ትምህርት አስተምሮ ፤ ላይመጣ ዳግመኛ
የግር እሳት ሆኖ ፤ ይፋጀል ግምኛ
ነበልባል ፤ እሳት ነው ፤ እንዳባቱ አርበኛ
ለወገኑ የሚሞት ፤ የሀገሩ እረኛ
የጠላት ፤ ደም ሳይረግጥ ፤ እንቅልፍም አማይተኛ ።

ፋሽስት ቢደነፋ ፤ ሰራዊቱን ከቶ
ሺውን ቢሰበስብ ፤ መለከት ተነፍቶ
ወጣት ከተነሳ ፤ ከተመመ ወጥቶ
ያጠብቀዋል እንጂ ፤ አይፈታ ቀበቶ
የኢትዮጵያ ወጣት ፤ አይቻል ተገፍቶ
አሳዶ ሳይመታው ፤ የገባበት ገብቶ
መቃብር ሳይሰደው ፤ አፈር ድሜ ፤ አብልቶ
አላማው ፤ ግብ ሳይደርስ ፤ አያርፍም ተኝቶ ።

ታዛቢው … March, 05, 2010